928

ፒስ አነስተኛ የገንዘብ ተቋም አክሲዮን ማህበር
የባለአክሲዮኖች 4ኛ ድንገተኛ ጉባኤ
ቃለ ጉባኤ ቁጥር 4

1. ጠቅላላ ጉባዔው የተደረገበት ቦታ፣ ቀንና ሰዓት

ቦታ:- አግሪሰርቪስ ኢትዮጵያ ዋና መ/ቤት የስብሰባ አዳራሽ (አዲስ አበባ)
ቀን:- 29/8/2008 ዓ.ም.
ሠዓት:- ከጠዋቱ 3:00 - 6:00 ሰዓት

2. የጉባኤው ጥሪ አደራረግ፣

ይህ የባለአክሲዮኖች 4ኛ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔ የተጠራው በንግድ ህግ አንቀጽ 392 መሠረት ሆኖ ከጉባዔው ዕለት 15 ቀናት አስቀድሞ በደብዳቤ ቁጥር PEACE110/16 በቀን13/8/2008 ዓ.ም በተፃፈ እና በአድራሻ በተላከ ደብዳቤ በተጨማሪም በስልክ ተጠርተዋል፡፡

3. የጉባኤው ጽ/ቤት አባላት እና በጉባኤው የተገኙ አስተዳዳሪዎች

3.1 የጉባኤው ጽ/ቤት አባላት፣

| ተ/ቁ | ስም | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | የጉባኤው ሰብሳቢ |
| 2 | ወ/ሮ ጸሐይ ጸጋዬ መከተ | ድምፅ ቆጣሪ |
| 3 | ወ/ሮ አለምነሽ ኃ/ማርያም ባዲሾ | ድምፅ ቆጣሪ |
| 4 | አቶ ተዘራ ከበደ በቀለ | ፀሐፊ |

3.2 በጉባኤው የተገኙ አስተዳዳሪዎች፣

| ተ/ቁ | የአስተዳዳሪዎች ስም | በአስተዳደር ምክር ቤት (ቦርድ) ውስጥ ያለው ኃላፊነት | የአስተዳዳሪው ወይም የተወካይ አስተዳዳሪ ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | የቦርድ ሊቀመንበር | |
| 2 | ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ | የቦርድ አባል | |
| 3 | አቶ ኤፍሬም አላምረው ቦጋለ | የቦርድ አባል | |

## 3.3 በጉባኤው ያልተገኙ አስተዳዳሪዎች፣

| ተ/ቁ | ስም | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ ፍላጐት ለማ ክብረት | አባል |
| 2 | ሲ/ር መሠረት ሺፈራው ይብራሁ | አባል |
| 3 | ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ ሰሚነው | አባል |
| 4 | አቶ ማሞ ከበደ ሽንቁጥ | አባል |

## 3.4 በጉባኤው የተገኙ ታዛቢዎች

| ተ/ቁ | ስም | የወከሉት ድርጅት |
|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ ተናኘ ተዘራ | ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሰነዶች ምዝገባ እና ማረጋገጫ ጽ/ቤት |
| 2 | አቶ ስለሺ ከበደ | ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሰነዶች ምዝገባ እና ማረጋገጫ ጽ/ቤት |

## 4. ምልዓተ ጉባኤ፣

4.1. ጠቅላላ የማኅበሩ አባላት ብዛት 16

4.2. ጠቅላላ የማኅበሩ የተፈረመ አክስዮን ብዛት 1,288

4.3. በስብሰባው የተገኙ አባላት ብዛት 10 የያዙት አክስዮን ብዛት 810 (63 %)

4.4. በስብሰባው ያልተገኙ አባላት ብዛት 6 የያዙት አክስዮን ብዛት 478 ( 37 %)

4.5. ለጉባኤው አስፈላጊ የሆነ የአክስዮን ብዛት 644 (50%)

በዚሁ መሰረት በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 22 እና በንግድ ህጉ አንቀጽ 425 መሠረት ከማህበሩ ባለአክስዮኖች 63% የተገኙ ስለሆነ በጉባዔው አጀንዳ ላይ ተወያይተው ውሣኔ ማሳለፍ ሥልጣን ያላቸው መሆኑ ተረጋግጦ ጉባዔው ቀጥሏል፡፡ በጉባኤው ላይ የተገኙትንና ያልተገኙትን ባለአክሲዮኖች ስም ዝርዝርና የያዙትን አክስዮን መጠን የያዘ ሠንጠረዥ (Attendance Sheet) (ሠንጠረዥ-1) ከዚህ ቃለ-ጉባኤ ሰነድ ጋር ተያይዟል፡፡

## 5.የጉባዔው አጀንዳዎች

5.1. የጉባኤውን አጀንዳ ማጽደቅ፣

5.2. በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 6 መሠረት የመተዳደሪያ ደንቡን አንቀጽ 12 (2) ማሻሻል እና

5.3. የማህበሩ ባለአክሲዮኖች በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የመገኘት ግዴታ በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ መጨመር፤

5.4. በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር MFI/27/2015 መሠረት የኩባንያውን ካፒታል ማሳደግ፣

5.5. የጉባኤውን ቃለ ጉባኤ ማጽደቅ ናቸው፡፡

6. የጉባኤው ውይይት አጭር ቃልና ውሣኔ፣

6.1 አጀንዳ 5.1 የጉባኤውን አጀንዳ ማጽደቅ

6.1.1 የውይይቱ አጭር ቃል

የጉባኤው ሰብሳቢ ጉባኤው ሊነጋገርባቸው ይገባል በማለት የቀረበውን አጀንዳ በዝርዝር በማስረዳት ጉባኤውን ሊጨመር ወይም ከአጀንዳ ሊወጣ የሚገባ ካለ በመጠየቅ ለውሳኔ አቅርበዋል፡፡

6.1.2 ውሣኔ፣

በአጀንዳው አስፈላጊነት ላይ ጉባኤው ከተነጋገረ በኋላ የቀረበውን አጀንዳ በቂ መሆኑን ተነጋግሮበት ጉባኤው ተወያይቶ ለመወሰን አጀንዳዎችን አፅድቋል፡፡

6.2 አጀንዳ 5.2. በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 6 መሠረት የመተዳደሪያ ደንቡን አንቀጽ 12 (2) ማሻሻል

6.2.1 የውይይቱ አጭር ቃል

ጉባኤው የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት የሥራ ዘመን እና በድጋሚ ስለመመረጥ መቻላቸው በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተቀመጠውን አንቀጽ ማሻሻልን በተመለከተ በጥልቀት ተወያይቶበት የንግድ ህጉን አንቀጽ 350(ንኡስ አንቀጽ 3እና4)ትን መሠረት በማድረግ የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12(2) ማሻሻል ለማህበሩ ጠቃሚ መሆኑ ታምኖበታል፡፡በዚህም መሠረት ደንቡን የመሻሻያ አጀንዳ ላይ ጉባኤው በጥልቀት ተወያይቶበት የዳሬክተሮች ቦርድ የሥራ ዘመን በንግድ ህጉ የተቀመጠው ከፍተኛው ሶስት ዓመት የሥራ ዘመን በመተዳደሪያ ደንቡ ቢካተት ተገቢ ስለመሆኑ ጉባኤው ተስማምቶ ነገር ግን የአባላቱ በድጋሚ መመረጥን በተመለከተ ገደብ ቢደረግ የተለያዩ ሰዎች ማህበሩን በቦርድ የማገልገል እድል ይኖራቸዋል ይህም ለባለአክሲዮኑ እና ለማህበሩ ጠቃሚ በመሆኑ በድጋሚ የመመረጥ ገደብ አስፈላጊነት ላይ ጉባኤው ሰፊ ውይይት አድርጓል፡፡ በውይይቱ ከተነሱ ሃሳቦች ዋና ዋናዎቹ የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት ላይ በድጋሚ መመረጥን አስመልክቶ ገደብ መጣሉ ማህበሩ አሁን ካለው ውስን ባለአክሲዮኖች የተነሳ ለቦርድ እጩ ሆኖ የሚቀርብ አባል የማጣት ስጋት ሊያጋጥመን ይችላል የሚለው አንዱ ሲሆን ሌላው ደግሞ የማህበሩን ባለአክሲዮን ቁጥር እንዲጨምር ማድረግ መፍትሄ አድርጎ በመውሰድ የቦርድ አባላቱ በድጋሚ ሊመረጡ የሚችሉበትን ጊዜ መወሰን አስፈላጊ ነው የሚል ነበር፡፡ በመጨረሻም የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12 (2) "የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት የሥራ ጊዜ ሁለት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም ለተከታታይ አንድ የሥራ ጊዜ ብቻ በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ" በማለት የተደነገገው ተሽሮ የኩባንያው ቦርድ የሥራ ዘመን ሶስት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም አባላቱ ከሁለት የሥራ ዘመን በኋላ በድጋሚ ለመመረጥ አንድ የሥራ ዘመን ማለፍ አለባቸው ፡፡ በሚል እንዲሻሻል ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቷል፡፡

6.2.2 ውሣኔ

የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12 (2) የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት የሥራ ጊዜ ሁለት ዓመት ይሆናል:: ሆኖም ለተከታታይ አንድ የሥራ ጊዜ ብቻ በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ:: በማለት ተደንግጎ የነበረው አንቀጽ :-

የማህበሩ ዳሬክተሮች ቦርድ የሥራ ዘመን ሶስት ዓመት ይሆናል:: ሆኖም አባላቱ ከሁለት የሥራ ዘመን በኋላ በድጋሚ ለመመረጥ አንድ የሥራ ዘመን ማለፍ አለባቸው ::በሚል እንዲሻሻል ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ውሳኔውን አጽድቋል::

6.3 አጀንዳ 5.3 የማህበሩ ባለአክሲዮኖች በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የመገኘት እና በዳሬክተሮች ቦርድ አባልነት የመመረጥ እና በቦርድ አባልነት ለተመረጡበት የሥራ ዘመን ማህበሩን የማገልገል ግዴታ በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ መጨመር፤

6.3.1 የውይይቱ አጭር ቃል

የጉባኤው ሰብሳቢ አጀንዳውን በማብራራት ጉባኤው እንዲወያይበት ያቀረቡ ሲሆን ከጉባኤው አባላት የባለአክሲዮኖችን በጉባኤ መገኘትን አስመልክቶ ግዴታ ማስቀመጡ ይበልጥ ማህበሩን የሚጎዳ ስለመሆኑ እንዲሁም ይህንንስ ግዴታ በባለአክሲዮኑ ላይ ለመጣል የህግ መሠረት አለው ወይ የሚል ጥያቄ ተነስቷል:: ማህበሩ ካለት አነስተኛ የጉባኤው ሰብሳቢ የባለአክሲዮኖች በስብሰባ አለመገኘት የባለአክሲዮኖች ቁጥር የተነሳ በባለአክሲዮኖች ላይ በ ጠቅላላ ጉባኤ የመገኘት ግዴታ በመተዳደሪያ ደንብ መካተቱ ማህበሩን ይጠቅማል በሚል አጀንዳ ሆኖ መቅረቡን ገልፀው የነበረ ሲሆን ሆኖም የጉባኤ አባላት በጉባኤ የመገኘት እና በቦርድ አባል ውስጥ የመመረጥ እና የማገልገል ግዴታ በመተዳደሪያ ደንቡ መጨመሩ ይበልጥ ባለአክሲዮኑን ከማህበሩ የሚያርቅ ነው በማለት በስብሰባ የመገኘት ግዴታ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መጨመሩ አስፈላጊ አይደለም በማለት ሃሳባቸውን አቅርበዋል::

በመሆኑም ጉባኤው የባለአክሲዮኖችን በጉባኤ የመገኘት ግዴታ በመተዳደሪያ ደንብ ስለማስገባት በተመለከተ አብዛኛውን ጊዜ የማይገኙ ባለአክሲዮኖች እንዲገኙ ከማበረታታት ወይንም ያላቸውን አክሲዮን በፍቃደኝነት ማህበሩን ሊጠቅም ወደሚችል በጎፍቃደኛ ተቋም ወይም ግለሰብ እንዲያስተላለፉ ከማድረግ ባለፈ ደንብ በማውጣት ያለፍቀዳቸው ከማህበሩ ማስወጣት መፍትሄ እንደማይሆን ነገር ግን የማህበሩን አባለት ቁጥር ማሳደግ ላይ መስራቱ ለማህበሩ ህልውና አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት የማህበሩ የዳሬክተሮች ቦርድ በተቻለ መጠን ትላልቅ የፋይናንስ ተቋማት ፒስን እንዲቀላቀሉ ጥረት እንዲያደርጉ የሚል ሃሳብ ተነስቷል:: በመጨረሻም የባለአክሲዮኖችን በጉባኤ የመገኘት እና በቦርድ ተመርጦ የማገልገል ግዴታን በተመለከተ በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የግዴታ አንቀጽ ለማስገባት የቀረበው አጀንዳን ጉባኤ በሙሉ ድምጽ ውድቅ አድርጎታል::

6.3.2 ውሳኔ
ጉባኤው በማህበሩ ባለአክሲዮኖች ላይ በጠቅላላ ጉባኤ የመገኘት እና በቦርድ አባል ውስጥ ተመርጦ የማገልገል ግዴታ በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ መጨመርን አስመልክቶ በቀረበው አጀንዳ ላይ ከተወያየ በኋላ በማህበሩ ባለአክሲዮኖች ላይ በጠቅላላ ጉባኤ የመገኘት ግዴታ እና በቦርድ የመመረጥ እና የማገልገል ግዴታ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ለማስገባት የቀረበው አጀንዳ በሙሉ ድምጽ ውድቅ ሆኗል በማለት ውሳኔውን አጽድቋል፡፡

6.4 አጀንዳ 5.4 በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር MFI/27/2015 መሠረት የኩባንያውን ካፒታል ማሳደግ

6.4.1 የውይይቱ አጭር ቃል
የማህበሩ ዳሬክተሮች ቦርድ የቀረበውን አጀንዳ በተመለከተ የብሔራዊ ባንክን መመሪያ ቁጥር MFI/27/2015 ጉባኤው እንዲመለከተው ያቀረቡ ሲሆን መመሪያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ማቋቋሚያ ዝቅተኛው የተከፈለ ካፒታል 10,000,000.00 (አስር ሚሊዮን ብር) እንዲሆን የሚደነግግ ሲሆን ነገር ግን በስራ ላይ ያሉት አነስተኛ የገንዘብ ተቋሞች አቅማቸውን ከግምት በማስገባት እ.ኤ.አ ከ ሰኔ 2015 ጀምሮ  እስከ ሰኔ 30/2021እ.ኤ.አ ድረስ ዝቅተኛው የተከፈለ ካፒታል 10,000,000.00 (አስር ሚሊዮን ብር) መሆን እንዳለበት የሚያስገድድ እና ይህንንም መስፈርት በማያሟሉ ተቋማት ላይ እርምጃ እንደሚወስድ ተደንግጓል፡፡

ፒስ አነስተኛ የገንዘብ ተቋም አ.ማ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የተቀመጠውን አነስተኛ ካፒታል መጠን በአንድ ጊዜ ማሟላት የሚችል ስለመሆኑ ከጉባኤው ሃሳብ ተንስቶ ነገር ግን  ማህበሩ በሥራ ላይ የቆየ ከመሆኑ አንጻር ካፒታሉ ወደ አስር ሚሊዮን ከሚያድግ ከዚህ በላይ እንዲያድግ ማድረጉ የኩባንያውን ገጽታ የሚያሳድግ ስለሆነ እና ለብድር የሚውል የብድር ፈንድ ከአበዳሪዎች ለማግኘት በአበዳሪዎች ተቋማት ዘንድ የካፒታሉ ማደግ ለማህበሩ ተቀባይነት የሚያስገኝለት በመሆኑ ካፒታሉ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር MFI/27/2015 ከተቀመጠው የአነስተኛ የገንዘብ ተቋማት አነስተኛ የተከፈለ ካፒታል በላይ እንዲሆን በጉባኤው ሰፊ ውይይት ተደርጓል፡፡

በመጨረሻም የአክሲዮን ማህበሩ አመታዊ ትርፍ ለባለአክሲዮኖች ሳይከፋፈል ለማህበሩ ስራ መልሶ የሚውል በመሆኑ ከምስረታው ጀምሮ ከተጠራቀመው የማህበሩ ትርፍ ተቀንሶ ብር 25,000,000.00 (ሃያ አምስት ሚሊዮን ብር) የተከፈለ የማህበሩ ካፒታል ሆኖ እንዲያድግ ጉባኤው  ስምምነት ላይ በመድረሱ የማህበሩ ካፒታል አሁን ካለበት 1,288,000.00 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት ሺ ) ወደ 25,000,000.00 (ሃያ አምስት ሚሊዮን ብር) እንዲያድግ በማለት ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ሙሉ ስምምነቱን ለውሳኔ አሳልፏል፡፡

| ተ.ቁ | ስም ክነአያት | የያዙት የአክሲዮን ብዛት | የአንድ አክሲዮን ዋጋ (በብር) | የተፈረመ አክሲዮን (በብር) | የተከፈለአክሲዮን (በብር) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቱ ወ/ማርያም | 2,453 | 1,000 | 2,453,000.00 | 2,453,000.00 |
| 2 | አቶ ማሞ ከበደ ሸንቁጥ | 2,453 | 1,000 | 2,453,000.00 | 2,453,000.00 |
| 3 | ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ | 2,452 | 1,000 | 2,452,000.00 | 2,452,000.00 |
| 4 | አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ | 129 | 1,000 | 129,000 | 129,000.00 |
| 5 | አቶ መስፍን ተፈራ ወ/ገብርኤል | 2,452 | 1,000 | 2,452,000.00 | 2,452,000.00 |
| 6 | ወ/ሮ ፀሀይ ፀጋዬ መኩተ | 2,452 | 1,000 | 2,452,000.00 | 2,452,000.00 |
| 7 | አቶ ኤፍሬም አላምረው | 2,452 | 1,000 | 2,452,000.00 | 2,452,000.00 |
| 8 | አቶ አክሊሉ ታደሰ አሻሚ | 25 | 1,000 | 25,000.00 | 25,000.00 |
| 9 | ወ/ሮ ሰላማዊት አበበ ተሜኔ | 81 | 1,000 | 81,000.00 | 81,000.00 |
| 10 | ወ/ሮ አለምነሽ ኃ/ማርያም ባዲሾ | 2,452 | 1,000 | 2,452,000.00 | 2,452,000.00 |
| 11 | ወ/ሮ ጽጌ ሃይሌ ወ/ጊዮርጊስ | 2,452 | 1,000 | 2,452,000.00 | 2,452,000.00 |
| 12 | ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ | 81 | 1,000 | 81,000.00 | 81,000.00 |
| 13 | ሲ/ር መሠረት ሺፈራው | 81 | 1,000 | 81,000.00 | 81,000.00 |
| 14 | ወ/ት ፍላጐት ለማ ክብረት | 81 | 1,000 | 81,000.00 | 81,000.00 |
| 15 | ወ/ሮ ለበሰች ጸጋ ባለሀ | 2,452 | 1,000 | 2,452,000.00 | 2,452,000.00 |
| 16 | አቶ ተዘራ ከበደ በቀለ | 2,452 | 1,000 | 2,452,000.00 | 2,452,000.00 |
| | ድምር | **25,000** | | **25,000,000.00** | **25,000,000.00** |

6.4.2 ውሣኔ

6.4.2 ውሣኔ

ጉባኤው የማህበሩ ካፒታል ቀድሞ ከነበረበት ብር1,288,000 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት ሺ) ወደ 25,000,000.00 (ሃያአምስት ሚሊዮን ብር )ከዚህ በላይ በተዘረዘረው መልኩ እንዲያድግ የተደረሰውን ስምምነት በሙሉ ድምጽ ወስኖ ውሳኔውን አጽድቆታል፡፡